# እኔና ፍራንክፈርት ክፍል ፪

በአዲስ ተስፋ

በመሰረቱ ከአገሬ ከወጣሁ በኋላ እንደዚህ አይነት የኢትዮጵያ መንግስት በሚያዘጋጀው የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ስብሰባ ተገኝቼ አላውቅም። የከፈልኩት መስዋእነትም የለም።ዶክተር አብይ ለውጥ አመጡ ፤ ህወሃትን በአፍንጫው ደፉት ከሚሉትም አይደለሁም። ቢሆንም ግን አንዳንድ የውሰዷቸውን እርምጃዎችና የሚያደርጓቸውን ንግግሮች ከሚያደንቁት እቀላቀላለሁ። ስለ ኢትዮጵያ ሲናገሩ ለቀባሪ አረዱት እንዳይሆንብኝ እንጅ በአትኩሮት እንደማዳምጣቸውና ግሩም አንደበተ ርቱዕ መሆናቸውን የሚክድ ስብእና የለኝም። በእለቱ ኦነጋውያን አለምን የተቆጣጠሩ የመሰላቸው ውሻ ጥራ አይነት ጬርቃቸው በስታዲዮም ስለተውለበለበና በተለይም የመድረክ መሪዎችን ስለያዙ ብቻ ነው።ሌላውና ጨዋው ኢትዮጵያዊ ቀን እንደሚያልፍ የተረዳና በጊዚያዊና ስሜታዊ የአሸናፍነት ስነልቦና የሚንቀጠቀጥ አልነበረም። እጅግ የገረመኝ ከኦሮሞ ውጬ የሆነው ህብረተሰብ ሳይሆን አብዛኛው ኢትዮጵያን ወዳድ ኦሮሞ በኦነጋውያን ድርጊት የተቃጠለ መሆኑ ነው። አማርኛ በደንብ የማትችል ብዙ አመት በኔዘርላንድስ የኖረች አንዲት ኦሮሞ ኢትዮጵያዊት ሙሉ ቀን ኢትዮጵያ ስትል ጉሮሮዋ እስኪዘጋ ድረስ ስትጮህ ማየቴ ለእኔ አስደናቂ ነበር። ይህች ሴት የኢትዮጵያን ባንዲራ ለብሳ በመካከላቸው እየገባች እናንተ ታሪካጩን የማታውቁ ባንዳ ሁላ በማለት በድፍረት ጻደብ ነበር። ኦነግ ውሸት ነው ፣ ኦነግ ወያኔ ነው እያለችም በድፍረት ትናገር ነበር። ሊሰድቧት ሲሞክሩ በኦሮምኛ በሃይል በመናገር ታሳፍራቸው ነበር። ብዙውን ጊዜ ኢትዮጵያ አሸናፊ ነች፣ ኢትዮጵያ የጀግና ህዝብ አገር ነች ፣ ጠላቶቻችን አይሰካላቸውም በማለት ታውራለች። በውስጤ እልቆ መሳፍርት የሌላቸው የኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ጭንቀትና ብስጭት ምን ያህል የበረታ መሆኑ ገባኝ። አንዳንዴ ኦሮሞ ሁሉ አንድ አይነት የሚመስለን ሰዎች ፈጽሞ ሽተት እንደሆንን በዘረኞችና በጎጠኞች የበቀል በትር የሚዎድቁትም አስቀድመው እንደዚህ አይነት ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን እንጂ ሌላው ህብረተሰብ ያለመሆኑን መረዳት ተገቢ ነው ባይ ነኝ። ፍራንክፈርት ጀርመን በነበረው ከዶክተር አብይ ጋር ውይይት ላይ ስለተነሱ ጥያቄዎች ሳይሆን ሰለ ስታዲይሙ ፕሮግራም እንዲሁም ከመድረክ ስለነበረው ሻጥር አውርቶ መጨረስ አይቻልም። ሰፊ በሆነው የኦሮሞ ህዝባችን ላይ ጸረ ኢትዮጵያዊ እንዲሆን የተነዛውን የበርካታ አመታት ፕሮፓጋንዳ ግን በቀላሉ የምናስወግደው አለመሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። ኦነግንና ጎጠኞችን የማባበል ዘመን ማብቃት አለበት። አንድ ልንረዳው የሚገባ ሌላ ብርቱ ጉዳይ ደግሞ የህወሃትን ወንጀለኞች ለመያዝና ለመቆጣጠር ዶክተር አብይ የሚቸገሩ ከሆነ ኦነግን ምንም ሊያደርጉት እንደማይችሉ ነው። ምክን ያቱም ኦነግ ላለፉት 40+ ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ ያልቻለ አሁንም ቢሆን ለዚህ ለታላቅ የኦሮሞ ህዝብ የማይመጥን የነፋስ ላይ አመድ ነው። ኦነግ ብእጁ ብዙ ወንጀሎች አሉ። የንጹሃን ደምም እውነተኛ ፍት ህን ይጣራል። በደልና ሃጢያቱ ይቅር ተብሎ ለፍት ህና እኩልናት ዘብ መቆም ባለበትና ውለእነተኛ ዲሞክራሲ መስፈን መታገል በሚገባው ጊዜ ግንድን ከስሩ ካልቆረጥኩ የሚል ቅዠት የሚቃዠ የስሜታውያን ስብስብ ነው። በነገራችን ላይ ፍራንክፈርት ጀርመን ይጠቀምባቸው የነበሩ ህጻናትና ወጣቶችን ነው። አብዛኛዎቹ ስለመገንጠልና ስለ ሚካሄደው ሻጥር ራሱ እውቀት አልነበራቸውም። የያዙት የኦነግ ባንዲራ ሲዎድቅባቸው ሮጠው የኢትዮጵያን ባንዲራ የሚይዙ ነበሩ። በርግጥ ቀሚስ አድረገውት የመጡ ሰቶች። ሙሉ ኮትና ሱሪ አሰፍተውት የመጡ ውጣቶችና ኮፍያ ያደረጉት ህጻናትም ነበሩ። ቢሆንም ገብቷቸውና ተረድተውት የያዙት ግን እጅግ ጥቂቶች በጣም አናሳዎች ነበሩ። ኦነግ ዘረኛና ጎጠኛ ብቻ ሳይሆን የበሰበሰና ተቆርጦ መጣል ያለበት በካንሰር የተጠቃ የሰውነት አካልን የመሰለ ከንቱ ስብስብ ነው። ለዚህ ማረጋገጫው አገራዊ አንድነትንና የዜጎችን ድጋፍ ተፈልጎ በተደረገ ስብሰባ ላይ በትንሹም ቢሆን ለማወክ መሞከር መድረክ መሪዎችን በማባበያም ይሁን በሌላ መንገድ መያዙ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ለሚመጡት እንግዳ ማለትም ለዶክተር አብይ ቅንጣት ያክል ከበሬታ አልነበረውም። እንደዚያ ቢሆንማ ኖሮ ካቢኔዎቻቸውና አምባሳደሮቻቸው የዲፕሎማሲ ድል ለማግኘት ኢትዮጵያውያንንም አንድነት አንድነት እንዲሸታቸው አርእስ መረጣ ጀምሮ በተዘጋጁበት በዚህ ፕሮግራም እንደዚህ ያለ ከፋፋይ ስራ አይሰራም ነበር።የኦነግ አባላት ወይም ደጋፊዎች ጋ የግል ቂም አልያም ጥላቻ ብዙዎቻችን የለንም። ችግሩ ያለው ካላቸው ትንሽ ሆኖ ትንሽ ካደረጋቸው ፖለቲካዊ አሜካከትና አይዶሎጂ ጋር ነው። ስለ አደዋ ጦርነት ስንት ኦሮሞ ጀግኖች እንደነገሱበትና በንጻሩ ስንቶቹ ኢትዮፖያ የሚለውን ባንዲራ ይዘው

ልዚህቾ አገር እንደተሰዉ  ብዙ ተተርኳል። በርካቶችም ምሁራን የሃገር ቤቶችም የውጭዎችም ጽፈዋል። ኦሮሞ ኢትዮጵያ ነው ኢትዮጵያም ኦሮሞ ነው። ነገር ግን በጎሳና በነገድ ፖለቲካ የታውሩ ሰዎች ጥንታዊውንና ብዙዎች የተረኩበትን መጽሃፍትም ሆኑ ሌሎች የታሪክ ድርሳናት ከማመንና ከመቀበል ይልቅ በተረት ተረት የተሞላዉንና በጥላቻ የሚያሰክረዉን የእነ ተስፋይ ገብረ አብ ድብቅ የፖለቲካ ፕሮግራም መቀበል ይቀላቸዋል። ሰዎች ስለ ተስፋየ  ስራዎች በአማራ ላይ ያለውን ጥላቻ የገለጸባቸው መጽሀፍት ናቸው  ይላሉ ። አዎ ያስኬዳል፤ ከዚያ በላቀ ሁኔታ ግን የኦሮሞን ታላቅነት የናቀበት ፣ኦሮሞ አዙሮ ማሰብ አይችልም በማለት የተሳለቀበት፣ ለኦሮሞ ህዝብ ዝቅተኝነቱን የሰበከበት መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ እንደሆነ ሌላው ቀርቶ ልሂቃን ነን የሚሉ እንኳ ያስተዋሉት አይመስልም። በለውጥ  ጎዳና እየነጎደ ነው የሚባለው በህወሃት ተጠፍትፎ የተሰራው የድሮው ኦህዴድ እንኳ ስለ ዝቅተኝነቱ አማራ ጡቴን ቆርጣል በሚል ልብዎለድ  በራሱ አንጡራ ሃብት የቆመለትን የጥላቻ ግንብ አላፈረሰም። ቀደሞ ነገር የሃገራችን ታሪክ የሁላችን ነው። ጉዲፈቻ የኦሮሞን ደስ የሚል ሰብአዊነት የሚያጎላ ባህል የኦሮሞ ብቻ አይደለም። የአማራውም  የጡት አባት ባህል የአማራው ብቻ ሊሆን አይችልም።ፍት ህና እኩልነትን የሚያጎላ  ለአለም እንዳበረከተ የምንተርክለት የገዳ ስርዓት አሁን ባለው ዘመናዊ የህግ ስርዓት ውስጥ አሻራውን ያስቀመጠውን የ በላ ልበልሃ ክርክርም ሁለቱም ኢትዮጵያን የሚያሳዩ ብርቅየ ባህሎቻችን ናቸው። በገዳ ኦሮሞ ይበልጣል በበላ ልበልሃ አማራ ይበልጣል ልንል አንችልም።በኢትዮጵያችን ደቦ፣ ወበራ፣ አፍርሳታና ሌሎችም ባህላዊና ሃይማኖታዊ ማህበራዊ ት ስ ስሮቻችን አንደኛውን ጎሳ የሚያተልቁ ወይም ሌላኛውን የሚያሳንሱ አይደሉም። እነዚህን  ሁሉ የሚያያይዙንን ሰንሰለቶች  የበጣጠሰው የኦነጋውያን ተንኮል በፍራንክፈርት ጀርመን ጎልቶ ለመውጣት ሙከራ አድርጎ ነበር። ነገር ግን የተሳካም የሆነም ነገር አልነበረም። ይህም በመጀመሪያ በኢትዮጵያውያን ትእግስት በኋላም በከተማዋ ምክትል ከንቲባና በዶክተር አብይ ንግ ግር አብዛኛው ህዝብ ታግሶ የሰላም ስብሰባ ሆኖ አልፏል።ለጊዜው የዶክተር አብይን ግልጽ ወይም የተደበቀ ፖለቲካዊ አቋማቸውን እንተወውና በእለቱ ያደረጉት ንግግር ግን ብ አርስ ብቻ ሳይሆን ጎጠኞች የቋመጡለትንና በመድረክ መሪዎች የሀገሪቱ የስራ ቋንቋ የተቀየረ  እስኪመስል ኦሮምኛን ብቻ ያነገሱበትን ውሏቸውን ቋጭተውታል።

የፍራንክፈርቱ ምክትል ከንቲባ በኢትዮጵያ ስላላቸው የኢንቨስትመት እቅድ፣ስለምስራቅ አፍሪካ የጸጥታ ጉዳይ ኢትዮጵያ ምን ያህል ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ እንዳላት፣ ስለተጫውተቸው፣ እየተጫወተች ስላለችውና ውደፊት ልትጫወታው ስላለ ሚና በሰፊውና በዝርዝር ተንትነዋል። ኢትዮጵያውያን ኩሩ ህዝብ፣ ለጠላት የማይንበረከኩና ለአለም  ሰላም ከፍተኛ አስተዋጽ ኦ እንዳደረጉም በታሪካዊ ማስረጃ በማስደገፍ ተናግረዋል። ኦነግን በመደገፍና ፖለቲካዊ አቅጣጫ በመስጠት የምትታማው ጀርመን ከፍተኛ ባለስልጣን ስለነበረው ግርግር ለመረዳት እንደማያቅታቸው  ቢታዎቅም ስለጎጠኛው ድርጅት አንድም ትንፍሽ አላሉም።ይልቁንም ስለኢትዮጵያውያን አንድነትና የገዘፈ ታሪክ ባለቤትነት አሳምረው ተርከዋል። ጀርመን አሉ ባለስልጣኑ በኢትዮጵያ ለተጀመረው ለውጥ ደጋፊ ብቻ ሳት ሆን  ሁኔታውን በቅርብ ትከታተላልች ብለዋል። የንግ ግራቸው አንድምታ ለውጥ እየተባለ ካለው የዶክተር አብይ እንቅስቃሴ ሙሉ መረጃ እንዳላቸውና አደናቃፊ የሚባሉትንም የሚያስጠነቅቅ ይዘት ነበረው። ለዚህ እንደ መረጃ መጥቀስ ካስፈለገ ዶክተር አብይ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኃላ የወሰዷቸው ጠንካራ ርምጃዎች ሃያላኑ ከጎናቸው እንደሆኑ የሚነገረውን ወሬ ከሃሜት በላይ ያደርገዋል። አውሮፓን ከጎበኙ  ብዙ ሳይቆዩ የተለያዩ ርዳታዎችና ብድሮች አግኝተዋል። የደህንነት ዋስትናቸውም የበለጠ አድጓል። በአሜሪካ በርካታ ኢትዮጵያውያንን በንግ ግራቸው አስፈንጥዘው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ  የጠበቃቸው ብዙም የተደላደለ ሁኔታ አልነበረም። የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ እንደተደረገባቸው፣ የግድያ ሙከራ እንደጠበቃቸውና ሃገሪቱ በከፍተኛ ያለመረጋጋት ሆና እንደነበር የምናስታውሰው ነው። በተቃራኒው አውሮፓን ጎብኝተው ሲመለሱ ግን ጉልበታቸው ጨምሮ፣ ወደ ስልጣን ተወዳጅና እውቅና ያላቸውን ሰዎች መቀላቀልና በርካታ ለለውጡ እንቅፋት ናቸው የተባሉ ሰዎችን ወደ እስር ቤት መላክ ሆኗል። የዚህ ጽሁፍ ቀንደኛ ተወቃሽ የሆነው ኦነግም በማይታመን ሁኔታ ረገብ ብሏል። እነ ጃዋር መሃመድም በማይታመን ፍጥነት ከሁሉን አዛዥነት ወደ ተስፋ ቆረጣነት ተሸጋግረዋል። አሁን ለውጡ ሊቀለበስ ነው አይነት ማላዘንም ጀምረዋል። ሌላው የዶክተር አብይ ድህረ አውሮፓ ጉብኝት ውጤት የ አማራ ክልል የሚባለው ከጥገኛ የህወሃት ተላላኪነት ወደ ዋና የሃገሪቱ የፖለቲካ ትኩረትነት መሸጋገሩ ነው። የዶክተር አብይ

በተደጋጋሚ ክልሉን መጎብኘት፣የተለያዩ ከተሞች ለምሳሌ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ደብረብርሃን፣ፍኖተሰላም፣ ኮምበልቻና የመሳሰሉት የራያን፣ መተከልንና ወልቃይት ጠገዴን የማንነት ጥያቄ እንዲሁም የላሊበላንና ጣናን ትኩረት ይሰጥ ትግል ማቀጣጠል በቀላሉ የሚናቁ ጥያቄወች አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ትናንት የኦሮሞ ደም የእኛም ደም ነው ብሎ ከጎንደር የዎጣውና ገዥዎችን ያርበደበደው የፖለቲካ ሙቀት ዛሬ ደግሞ የአፋሩ ደም የእኛም ደም ነው ብሎ ብቅ ማለቱ ነገር አለ እንድንል ብቻ ሳይሆን ለበርካታ አገራዊ ውይይቶች መነሻ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። አማራ የሚባለው ክልል የፖለቲካ ማእከል እንደሆነ ሌላም ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል። የሶማሊያውና የኤርትራው ፕሬዚዳንቶች ጉብኝት በተለይም ደግሞ ኢሳያስ አፎርቂ ያደረጉት ንግ ግር  የጠቀሳል ። ብቻ የዶክተር አብይ የአውሮፓ ጉብኝት አንዳች ለውጥ ይዞ የመጣ ይመስላል። ለአንባቢዎቼ  የፍራንክፈርት ምክትል ከንቲባ በዶክተር አብይ ጉብኝት ወቅት ያደረጊትን ንግ ግር ከዩቱብ እንድሰሙ እየጋበዝኩ ለማጠቃለያ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ስላሏቸው አንዳንድ ሃሳቦች ላንሳና ልጨርስ። ተስፋና ስጋት ከፊት ለፊታችን አለ። ተስፋችን በአንድነታችን ውስጥ ነው ። እጅ ለእጅ በመያያዝ መንደርና ሰፈሬ የሚለውን በሽታ ጥለን አንዲት ታሪኳን የጠበቀች የበለጸገችና ለልጅ ልጆቻችን የምትመች ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ሲሆን ስጋታችን ደግሞ ነጻነታችን አንድነታችንና ባለብዙ አመት ታሪክ መሆናችን ያልተዋጠላቸው በማበጣበጥና በማጋጨት ብቻ ህልውናቸው የሚጠበቅ የሚመስላቸው ጸረ ለውጥ ሃይሎች ናቸው ብለዋል። ኢትዮጵያ አሉ ዶክተር አብይ

'' ኢትዮጵያ ማንም ተነስቶ በወደደው መልክና ልክ እንደ ቂጣ ጠፍጥፎ የሚጋግራት የግል ርስት ሳትሆን ዘመናትን ያስቆጠረች ታላቅ ህዝብ የመሰረታት ታላቅ አገር መሆንዋን ነው። እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጎበኘው እንዲሉ ሀገሬ አንቀላፍታ ይሆናል እንጂ አልሞተችም፣ኢትዮጵያ ደክማ ይሆናል እንጂ አልተሸነፈችም፣ እምየ ቀጥና ይሆናል እንጂ አልተበጠሰችም''

ይህ ንግ ግራቸው ብዙ ኢትዮጵያውያንን ቢያስፈነጥዝም በተንኮል ተወሮ ለዋለው መድረክ ግን ድንገተኛ ውርጅብኝ ይመስል ነበር። ለማንኛውም ሙሉ ንግ ግራቸው አስደናቂ እንደነበር መመስከር የግድ ነው። ኦነጋውያን ግን ደስተኞች አልነበሩም። የሆነው ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ እየወሰዷቸው ያሉ እርምጃዎች በሙሉ በፍራንክፈርት ቃል የገቡትን እየፈጸሙ ያሉ ይመስላል። ቱባ ቱባ የህወሃት ጀነራሎችም ወደ እስር ቤት መወርወር ጀመረዋል። አሁን ጨዋታው ሁሉ አበቃ በማለት የምንቀመጥበት ጊዜ ግን አይደለም። ዛሬም ህወሃታዊያንና ኦነጋውያን ጠላታቸው አማራ እንደሆነ እየሰበኩ ነው።በሞት ጣር ላይ ነው ላራሱ መሟገት የገባዋል የምንለው ወያኔ ዛሬም ለአብዲ ኢሌ፣ ዛሬም በሻጠር ላደራጃቸው የቅማንት ማንነት አባላት ሰብዓዊ መብት መጣስ፣ ዛሬም ስለ አማራ ጠላትነት ይሰብካል።

በአይጋ ፎረም በ15/11/1/2018 ዓም ፍስሃ መረሳ በተባሉ ሰው '' ድራማው ለተመልካቹ ግልፅ ነው '' በሚል ርዕስ በተጽፈ ጽሁፍ የሚከተለውን እናነባለን። '' **አሁን አንዱ የድራማ ገፀባህሪ የመንግሥት ሃብት የዘረፉ ሰብአዊ መብት የጣሱ ተይዘዋል ይላል የፌዴራል አቃቤ ህግ ሪፖርት ፡፡ ግን መንግሥት በእውነቱ ወንጀሎች ለመያዝ የሚያስችል ቁርጠኝነት አለው ? ይህን ለማየት ኣንዳንድ ማሳያዎች ብናነሳ ጥሩ ይሆናል ፡፡ ከሁሉም በፊት መንግሥት ማንኛውም ህግ ጥሶ ሰብዓዊ መብት የተጋፋ የህዝብ ሃብት የዘረፈ ለመቆጣጠር ፍላጎት ካለው ለምንድነው ነው በቢልዮን የሚገመት ሃብት መንግሥት እንዲያጣ ያደረጉ ከዚህም በፊት በቁጥጥር ስር የዋሉት የጉምሩክ ባለስልጣናትን ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈቱ ያደረገው ? የሜቴክና የጉምሩክ ባለሥልጣናት ሁሉም ኢትዮጵያውያን አይደሉም እንዴ ? ለፖለቲካ ትርፍ ተፈልጎ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም የድሃው ህዝብ ሃብትና ንብረት ያባከኑ አይደሉም እንዴ ? እንድያውም የበፊቶቹ በፍርድ ቤት ቀርበው ጥፋተኛ ተብለው እያሉ ህገመንግስታዊ ስርአቱ በማይፈቅደው መንገድ የተለቀቁት ለምን ይሆን ? እኔ አልነበርኩበትም እና ከኔ በፊት የነበረ ሁሉ ስራ ቆሻሻ ነውና ህዝብና መንግሥት ቢጎዱም እኔ አያገባኝም ካልተባለ በስተቀር ትናንት ሌቦችን የለቀቀ**

መንግሥት አሁን ፀረ ሌቦች ተነስቻለሁ ቢለን በየትኛው መመዘኛ ነው ይህ ውሳኔ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው ?

ሌላው  እየተነገረን ያለው አዲሱ ፋሽን በሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚጠየቁ ስላሉ በቁጥጥር አውለናል ይላል መግለጫው ፡፡ በዚህ በኩልም የተሰራው ድራማ በጣም አስቂኝ የሆነና ማንም በቀላሉ ሊረዳው የሚችል መሆኑ ግልፅ ነው ፡፡ ለማሰር የተፈለገ ሰው ለመያዝና ይዞ ለማጥቃት ስለተፈለገ እንጂ ስንት ወንጀለኛ የዜጎች ሂወት የቀጠፈ በዘረኝነት አነሳስቶ ሆን ብሎ ህዝብ ለህዝብ እንዲጋጭ ያደረገ የህዝብና የመንግሥት ሃብት ያወደመ እንዲያውም በሰብአዊ መብት መርማሪ ኮምሽን ተለይቶ በህግ እንዲጠየቁ የተለዩ **ለአብነት የአማራ መንግሥት ባለሥልጣናት በቅማንትና በትግራይ ተወላጆች በፈፀሙት የዘር ማጥፋት ስራ እንዲጠየቁ ውሳኔ ተላልፎ እያለ ከነዚህ በላይ ማን ሰብዓዊ መብት** ጥሰት ፈፅሞ ነው አሁን በቁጥጥር አውለናል እየተባለ ያለው ?
በአሁኑ ሰአት በየአካባቢው ዜጎች ያለ ፍርድ በጠራራ ፀሃይ በአደባባይ እንደእንስሣ ታርደው በሚገደሉበት ኣገር በአስከፊ ሁኔታ ያለ ጥፋታቸው በደቦ ፍርድ በድንጋይ ተደብድበው እየተገደሉ እነዚህ ወንጀሎች ተቆጣጥሮ ህግ ፊት ማቅረብ ያልቻለ መንግሥት ማንን ለማታለል ታስቦ ነው አሁን ከአንገት በላይ በመጮህ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ መስሎ
የሚቀርበው ፡፡ አንድ ሌላ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነገር በስልጣን ላይ ያለው ሃይል ሳይጣራ ሰው አይያዝም የሚል ስልት ደጋግሞ ሲጠቀምበት ይታያል ፡፡ እስኪ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ፕረዚዳንት ህገመንግስታዊ ስርአቱ አፍርሶ ራሱ በወታደራዊ ሃይል ተቆጣጥሮ እስር ቤት አስገብቶ ሲያበቃ እስካሁን ከሶስት ወር በላይ ክስ ሳይቀርብበት በቀጠሮ መከራውን እያየ ጥቃት እየተፈፀመበት እንዳለ በተግባር እየታየ ያለ ሃቅ እያለ ማንን ለማታለል ይሆን ሳናጣራ አንይዝም የሚባለው ?’’

በዚህ ጽሁፍ ብዙ የሚገራርሙ ነገሮች ቢኖሩም የመላኩ ፈንታ መፈታትን በጽኑ ይቃውማል፣ ቅማንትና ትግሬን የገደሉ የአማራ ባለስልጣናት ለምን አልታሰሩም ይላል አብዲ ኢሌ ወንጀል የለበትምና እጅግ በርካታ አሳዛኝ ነገሮች ተካተውበታል። አገውንና አማራን ቅማንንትንና አማራን ለማፋጀት በዚህን የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ቢቻል ቅማንትንና አገውን ይዞ የመገንጠሉ አጀንዳ ገና ያልተቋጨ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። አገው በሚገባቸው መንገድ ነግሯቸዋል፣ የተወሰኑና በገንዘብ የሚንቀሳቀሱ ከ አምስት የማይበልጡ የቅማንትን ማህበረሰብ እወክላለሁ የሚሉ ከሃዲዎች ግን ዛሬም አሉ። በጊዜ በምገባቸው ቋንቋ ሊነገራቸው ይገባል። ሌላው የአይጋ ፎረም ጸሃፊ አማራን እንዲህ ሲያብጠለጥሉ ኦነግ የምትል ቃል ግን ፈጽሞ አልተጠቀሙም።  በዚሁ በተመሳሳይ ቀን አቶ በቀለ ገርባ በነቀምት ባደረጉት ን ግ ግር ለኦሮሞ እየታገለ ያለው የኦነግ ወታደር ብቻ ነው ፣ህወሃት ከሌሎች በተለየ ለ አገሪቱ ስጋት ነው ብየ አላምንም ብለዋል።

ጆሮ ያለው ይስማ በማለት እኔና ፍራንክፈርትን በዚህ እቋጫለሁ።

© አዲስ ተስፋ